# የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን

## የ2018በጀት አመት ዕቅድ

user

ኢግባ

ግንቦት 2017

ማውጫ ገጽ

1. መግቢያ ..... 4
1.1 የእቅዱ አስፈላጊነት ..... 4
1.2 የእቅዱ መነሻ ..... 4
1.3 የባለሰለጣኑ ተልዕኮ፣ ራዕይና እሴቶች ..... 5
1.3 የባለስልጣኑ ስትራቴጅክ ግቦችና /ቁልፍ ተግባራት በፕሮግራሞች ..... 6
1.4 የሁኔታዎች ትንተና (SWOT Analysis) ..... 7
የነበሩ ጠንካራ ጎኖች ..... 7
መልካም አጋጣሚዎች ..... 7
ስጋቶች ..... 8
2. የ2017 በጀት አመት የዕቅድ አፈጻጸም ..... 8
3. የ2018 በጀት አመት ዕቅድ ..... 8
3.1 የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቁጥጥር ማጠናከር ..... 9
3.1.1 ውጤታማነቱ ተረጋግጦ የብቃት ማረጋገጫ ያገኙ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ ..... 9
ለ ..... 9
3.1.2 በኢንስፔክሽን ብቃታቸው የተረጋገጠ የምርምር፣ የኤክስቴሽንና የመካናይዘሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ..... 9
3.2 የእጽዋት ግብዓቶች ምርቶች እና አገልግሎት ቁጥጥር ማጠናከር ..... 9
3.2.1 ፍቱንነቱ፣ደህንነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ የፀረ ተባይ እና የአፈር ማዳበሪያ ..... 9
3.2.1.2 ጥራቱ የተረጋገጠ የአፈር ማዳበሪያ ..... 9
3.2.2 ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ለውጭ እና ለሀገር ውስጥ ገበያ የቀረቡ የዕጽዋት ምርቶች ..... 10
3.2.2.1 ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ዕጽዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች ..... 10
ለ 960,000 ሜትሪክ ቶን የዕፅዋት ዉጤቶች ጤንነቱ፣ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ እንዲላክ ይረጋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ቀጣዮቹ ዝርዝር ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ ..... 10
3.2.2.2 ጤንነቱ፣ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕፅዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች ..... 11
3.2.2.4 የእፀዋት ዝርያ ጥበቃና ዘር ጥራት ቁጥጥር ..... 12
በምርምር ቀርበው የተገመገሙ ዕጩ የዕፅዋት ዝርያዎች ..... 12
3.2.2.5 ደረጃውን የጠበቀ የእፀዋት ጥራት ምርመራ ላብራቶሪ አገልግሎት ..... 12

3.2 የእንሰሳት ግብዓቶች ምርቶች እና አገልግሎት ቁጥጥር ማጠናከር ..... 13
3.3.1 የእንሰሳት ምርቶችን ጤንነት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ ..... 13
3.2.2 በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች 14
3.2.3 ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድኃኒት ..... 15
3.2.4 ጥራትና ደህነነቱ የተረጋገጠ የእንሰሳት መኖ ..... 15
3.3.4.1 የመኖ ተቋማትና ባለሙያዎች የተሰጠ የብቃት ማረጋገጥ ..... 15
3.3.4.2 ጥራትና ደህንነቱ ተጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ መኖ እና የመኖ ግብዓት ..... 16
3.3.4.3 የእንሳሰት መኖ እና ተቋማት ላይ ኢንስፔክሽን ማካሄድ ..... 16
3.2.5 ደረጃውን የጠበቀ የእንሰሳት ጥራት ምርመራ ላብራቶሪ አገልግሎት ..... 16
4. ተቋማዊ የመፈፀም አቅም፣ ውጤታማ የሀብት አጠቃቀምና አገልግሎት አሰጣጥ እና የህግ ማዕቀፎች ..... 16
4.1 የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማጠናከር ..... 17
4.2 ተግባራዊ የተደረገ የህግ ማዕቀፍ ..... 18
4.3 በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (Digitalization) የታገዘ አገልግሎት ..... 19
4.4 ክትትልና ግምገማ ..... **Error! Bookmark not defined.**
ማጠቃለያ ..... **Error! Bookmark not defined.**
የ2017 በጀት ዓመት ቀጣይና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ..... **Error! Bookmark not defined.**

**ደርሞ**

*የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የግብርና ምርቶችን፣ግብዓቶችንና ፣ አገልግሎቶችንና የግብርና ቴክኖሎጂ፣ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቁጥጥር ስራዎችን እንዲያከናውን ስልጣን የተሰጠው የግብርና ቁጥጥር ተቋም ነው።ባለስልጣኑ በሁለት ዋና ዋና የቁጥጥር ፕሮግራሞች ማለትም በዕጽዋት ቁጥጥር ዘርፍ እንዲሁም በእንስሳት ቁጥጥር ስር ባሉ ክፍሎቹ የተደራጀና ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የሚሀድ የቁጥጥር ተግባትን እያከናወነ ሲሆን ከነዚህ ዘርፎች በተጨማሪም የግብርና ሜካናይዜሽን ፣ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጂ ቁጥጥር ስራ ለማስጀመር እየሠራ ይገኛል ። ይህ የዕቅድ ሰነድ በተለይም የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ መሠረት ባደረጉ የቁልፍ ተግባራት አመልካቾች ላይ የተመሠረተ ነው። ይህ ዕቅድ የአጠቃላይ የግብርና ሴክተር ዕቅድ አካል ሲሆን ወቅቱን የዋጀ የክትትልና ግምገማ ስርዓትን በመከተል እንዲሁም ከሁሉም ባለድርሻና ከአጋር አካላት ጋር በቅንጅት የሚከናወን ይሆናል።*

## 1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በ2021 በፌዴራል ፓርላማ በአዋጅ ቁጥር 1263/2021 አንቀጽ 11 ላይ በመመስረት ስልጣኑ እና ሚናው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 509/2022 ተለይቷል። ባለስልጣኑ በዋናነት የቁጥጥር ተግባራት መሠረት በማድረግ በዋና ዋና ምርቶችና አገልግሎቶች ማለትም የግብርና ቴክኖሎጂዎች፣ የግብርና ግብአቶች፣ የግብርና ምርቶች እና የግብርና አገልግሎቶች ደረጃቸውን የጠበቁ፣ የተመዘገቡ እና የምስክር ወረቀት ብቃት ባለው ሰው የሚመሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው። የግብርና ምርቶች እና አገልግሎቶች የአፈጻጸም/ውጤታማነት፣ የጥራት፣ የጤና እና የደህንነት ደረጃዎችን የሚያከብሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተከታታይ ምርመራዎችን ያደርጋል እንደ አስፈላጊነቱ የቁጥጥር እርምጃዎችን ይወስዳል።

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የ10 ዓመትና የመካከለኛ ዘመን የግብርና ሴክተር ዕቅድ አካል የሆነውን የግብርና ሬጉላቶሪ ዕቅድ መሠረት በማድረግ የ2018 ዓመታዊ ዕቅድ ዝግጅት ስራ አጠናቋል። በዕቅድ ዝግጅቱ ወቅት ታሳቢ ከተደረጉ ጉዳዮች መካከል በ2017 የተገኙ ተሞክሮዎች ዋናውን ድርሻ የያዙ ሲሆን ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችም ታሳቢ ተደርገዋል። የተጀመሩ ቅንጅታዊ አሠራሮች እንዲሁም ወሳኝ የሆኑና ለቁጥጥሩ ጥራትና ቅልጥፍና እገዛ የሚያደርጉ፣ በስትራቴጂክ ዕቅዱም በዋናና ልዩ የትኩረት መስክነት የተያዙ፣ እንደ ዲጂታይዜሽን ፣የህግ ማዕቀፍ ማሻሻያ ስራዎችን ታሳቢ ያደረገና ባለው የሰው ሀይልና ሌሎች ሀብቶች ተጠቅሞ ሊደረስበት የሚችል ዕቅድ አዘጋጅቶ አቅርቧል።

### 1.1 የእቅዱ አስፈላጊነት

እንደ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን በየጊዜው ሊለካ የሚችል ግብ በማስቀመጥ በ10 አመት እንደርስበታለን ብለን ያቀድነው ግብ ላይ ለመድረስ በየአመቱ እቅዳችን ሊራመድ የሚችልና አሳታፊ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል ይህንንም መነሻ በማድረግ በአመቱ ስኬታማ ሊሆን የሚችል ፣ሊለካ የሚችል እንዲሁም በምን ያህል መጠን ይሳካል? የሚለውን በየጊዜው ለመከታተል ያመች ዘንድ ይህ አመታዊ እቅድ ማዘጋጀት አስፈልጓል።

### 1.2 የእቅዱ መነሻ

ዕቅዱን ዉጤታማ ለማድረግ ከዚህ በፊት ያጋጠሙ ችግሮች እና መልካም እድሎችን በሚገባ መመርመርና እንደ ግብረመልስ ተጠቅሞ ለዕቅድ መነሻ ማድረግ በጣም ጠቃሚ መሆኑ ይታመናል። በዚህ መሠረት የ2018 በጀት አመት የግብርና ባለስልጣን እቅድ እንደመነሻ አድርጉ የያዘው

- የግብርና ሚኒስቴር የ10 አመት እና የመካከለኛ ዘመን እቅድ
- የባለስለጣኑ የ10 አመት እና የመካከለኛ ዘመን እቅድ
- የባለስልጣኑን የ2017 በጀት አመት አፈጻጸም
- በተለያየ ደረጃ የተደረጉ ግምገማዎችና የተሰጡ ግብረ መልሶች

- ባለስልጣኑ አሁን ባለበት ደረጃ ያለውን የሰውና ሌሎች ሀብቶች እንደ መነሻ ለመጠቀም ተችሏል፡፡

## 1.3 የባለሰለጣኑ ተልዕኮ፣ ራዕይና እሴቶቸ

**ተልዕኮ**

የግብርና ቴክኖሎጂ፣አገልግሎቶችን ግብዓቶችና ምርቶችን ጥራት፣ደህንነት፣ፍቱንነት፣ ፈዋሽነት፣ጤናማነትና ቀልጣፋነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል፤መልካም ስም ያለውና ፣ለአካባቢ ጥበቃ ተገቢውን ትኩረት የሚሰጥ የቁጥጥር ተቋምና ስርዓትን በመገንባትና የግብርና ቁጥጥር ስራዎችን በመተግበር፣ የግብርና ምርቶችን የሀገር ውስጥ እና የአለም ገበያ ተደራሽነትና ተወዳዳሪነትን በማሳደግ ለላቀ ሀገራዊ ጥቅምና የኤኮኖሚ ዕድገት የሚጠበቀትን አስተዋፅኦ ማበርከት፡፡

**ራዕይ**

በአለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅናና ተቀባይነት ያለው የግብርና ተቆጣጣሪ ተቋም መሆን

**እሴቶች**

Loyalty ታማኝነት

- Confidentiality/ሚስጥር ጠባቂነት
- Commitment አገልጋይነት
- Rule of the law /የህግ የበላይነት
- Accountability /ተጠያቂነት

•Customer focus ደንበኛ ተኮር አገልግሎት

- Impartiality /አለማዳላት
- Partnership /ትብብር
- Transparency. /ግልጽነት
- Responsiveness /ምላሽ ሰጪነት

## 1.3 የባለስልጣኑ ስትራቴጅክ ግቦችና /ቁልፍ ተግባራት በፕሮግራሞች

### ውጤታማነቱ፣ ጥራቱና ተስማሚነቱ የተረጋገጠ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ

- ውጤታማነቱ ተረጋግጦ የብቃት ማረጋገጫ ያገኙ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ
- በኢንስፔክሽን ብቃታቸው የተረጋገጠ የምርምር፣ የኤክስቴሽንና የመካናይዘሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት

### የእፀዋት በዕጽዋትና ፣ከእፀዋት ጋር በተገናኙ ግብዓቶች፣ ምርቶች፣ ቴክኖሎጂ እና አገልግሎቶች ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር ማጠናከር

- ፍቱንነቱ፣ደህንነቱ እና ጥራቱ የተረጋገጠ ፀረ-ተባይ እና ማዳበሪያ
- ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ለውጭ እና ለሀገር ውስጥ ገበያ የቀረቡ የዕጽዋት ምርቶች
- የዕጽዋት ዝርያ ጥበቃ እና ዘር ጥራት ቁጥጥር
- ደረጃውን የጠበቀ የእፀዋት ጥራት ምርመራ ላብራቶነሪ አገልግሎት

### የእንስሳትና ከእንስሳት ጋር የተገናኙ የግብዓቶች፣ ምርቶች፣ ቴክኖሎጂ እና አገልግሎቶች ቁጥጥር ማጠናከር

- የእንስሳት ምርቶችን ጤንነት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ
- በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች
- ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድኃኒት
- ጥራቱና ደህንነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መኖ
- ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳት ጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ አገልግሎት

### ተቋማዊ የመፈፀም አቅም ግንባታ፣ ውጤታማ የሀብት አጠቃቀምና አገልግሎት አሰጣጥ እና የህግ ማዕቀፎች

- የአቅም ግንባታ ሥራዎች
- የህግ ማዕቀፎችን ማዘጋጀት ማሻሻል
- የሃብት አጠቃቀምን ማሳደግ እና ሃብት ማፈላለግ
- የእቅድ ክትልና ግብረ መልስ ሥራዎችን ማከናወን
- ተቋማዊ አገልግሎትን ማሻሻል
- ሥርዓተ ጾታና ማህበራዊ አገልግሎት መተግበር
- ተቋማዊ ዲጅተላይ"ዘሽን አገልግሎት መስጠት
- ተቋማዊ ሪፎርም አተገባበር
- አጋርነት እና ህዝብ ግንኙት
- ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና

## 1.4 የሁኔታዎች ትንተና (SWOT Analysis)

**የነበሩ ጠንካራ ጎኖች**

- በስራ ላይ ያለውን የሰው ሀይል በስራ ቦታው ላይ መድቦ ማሰራት መቻሉ፣
- የእንስሳት ግብአት እና የምርት ጥራት ምርመራ ላብራቶሪ መኖር፣
- በአገር አቀፍ ደረጃ የተፈቀዱ ህጎች፣ የፕሮቶኮሎች ደረጃዎች፣ ቴክኒካዊ መመሪያዎች በተወሰኑ ቁጥጥር ስር ባሉ ግብአቶች እና ምርቶች ውስጥ መኖር
- ወደ ዲጅታላይዜሽን አሠራር ሥርዓት የተሻጋገሩ የምዝገባና ሰርትፊኬት አሰጣጥ ሥርዓቶች ጅምር መኖር ፣
- የተለያዩ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ስልጠናዎች መሰጠታቸው፣
- የቡድን ሥራን ለማሳለጥ የተሰጡ የተለያዩ የሥልጠናና የአቅም ግምባታ ስራዎች መከናወናቸው፣
- የቁጥር ስራዎን ለማዘመንና ተደራሽ ለማድረግ አመራር ቁርጠኝነት መኖሩ፣
- መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በጋራ ተቀናጅቶ መስራት መቻሉ፣
- ፖሊሲዎችን፣ አዋጅ፣ ደንቦች እና መመሪያዎችን በማዘጋጀት የተወሰኑት በመጽደቅ ሂደት ላይ ቢሆኑም የፀደቁትን ለሚመለከታቸው አካላት የማስተዋወቅ ስራ መሰራቱ፣

**ደካማ ጐኖች**

- በተወሰኑ የግብርና ቴክኖሎጂዎች፣ አገልግሎቶች፣ ግብዓቶች እና ምርቶች ላይ የተጠናከረና የጸደቀ የህግ ማዕቀፍ አለመኖርና የማጽደቅ ሂደቱ መርዘም
- ተቀባይነት ያለው የዕጽዋትና የእንስሳት ሬጉላቶሪ ስራ ለመስራት የሚያስችል የሰው ሀይልና ሎጅስቲክ አቅም ክፍተት በፌደራልም ሆነ በማዕከል ደረጃ መኖር.
- የዕፅዋት ግብዓት እና ምርት ምርመራ ላቦራቶሪውን አቅም በመገንባት እውቅናና ተቀባይነት ያለው የምርመራ ማዕከል ለማድረግና የክልል ላቦራቶሪዎች የጥራት ፍተሻ አቅም ለመገምገም የሚያስችል ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያገኘ (Accredidated) ላቦራቶሪ ያለመኖሩ.
- በድህረ ጥራት ፍተሻ ጣቢያዎች የቁጥጥር ስራቸውን በስታንዳርዱ መሰረት ለመስራት የሚያስችል የቁሳቁስና የመሰረተ ልማት ክፍተት መኖሩ፡፡
- የሀብት እጥረት መኖር የሚሉት ይገኙበታል፡፡

**መልካም አጋጣሚዎች**

- መንግስት ለግብርና ግብዓት እና ምርቶች ጥራት ቁጥጥር በተሰጠው ትኩረት የኢትዮጰያ ግብርና ባለስልጣን መመስረቱ፣
- ከክልሎች ጋር በትብብር መስራት መቻሉ፣
- ሀገሪቱ በየደረጃው ከሀገራት ጋር የፈጠረቻቸው ዲፕሎማሲያዊና የትብብር ሁኔታዎች ለወጪ ንግድ ቁጥጥር አመቺ ሁኔታ መፍጠራቸው፣

**ስጋቶች**

- የተጠናከረ ላብራቶሪ ባለመኖሩ ከውጪ የሚገቡ የግብርና ግብዓት እና ምርቶችን ብቃት፣ ጥራት ፣ ደህንነት ፣ ፍቱንነት እና ጤንነት ለማረጋገጥ ተፈላጊው አቅም አለመግንባቱ.
- የግብርና ቴክኖሎጂ እና ግብዓት ብቃት እናፍቱንነት የሚፈተሽበት የሙከራ ቦታዎች ማግኘት አለመቻል፤
- ለቁጥጥር ተግባራት የሚያስፈልጉ የህግ ማዕቀፎች ፀድቀው ወደ ሥራ የሚገባበት በተለያዩ ምክንያቶች መርዘም፣
- ባለስልጣኑ የራሱ የሆነ ቢሮ አለመኖሩ/ ኪራይ መሆኑ/፣

**2. የ2017 በጀት አመት የዕቅድ አፈጻጸም**

የ2017 በጀት አመት የቁልፍ አመልካቾች የእቅድ ክንውን በዚህ ሪፖረት መጨረሻ ላይ ባለው ሰንጠረዥ ላይ ለ2018 እቅድ መነሻ ሆኖ ተመላክቷል፡፡

**3. የ2018 በጀት አመት ዕቅድ**

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የአንድ ዕቅድ አንድ ሪፖርት አቀራረብ የሚከተል ሲሆን የአስር ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅዱን መሠረት በማድረግ የሚከናወኑና በ4 ፕሮግራሞች ፣በ9 ስትራቴጂክ አላማዎች እንዲሁም እነዚህን ስትራቴጂክ አላማዎች ለማሳካት በሚከናወኑ ቁልፍ አመልካቾች የተመሠረተ ነው ፡፡ይህንን መሠረት አድርጎም የባለስልጣኑ የ2018 ዕቅድ በፕሮግራሞች በስትራቴጂክ አላማዎች እንዲሁም በቁልፍ አመልካቾ ላይ መሠረት ያደረገ ዕቅድ እንደሚከተለው ቀረቧል፡፡

### 3.1 የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቁጥጥር ማጠናከር

#### 3.1.1 ውጤታማነቱ ተረጋግጦ የብቃት ማረጋገጫ ያገኙ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ

ለ 30 የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ ተቋማት ውጤታማታቸው ፣የጥራትና ተስማሚነቱ ሁኔታቸውን በማረጋገጥ የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዷል።ከዚህ ጋር ተያይዞም ቀጣዮቹ ዝርዝር ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል።

- ✓ ለ10 ሬጉላቶሪ ስራዎችን በማከናወን የግብርና መሳሪያ የቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ መስጠት፣
- ✓ 20ግብርና መሳሪያ ጥራት በሰነድ ግምገማ በማረጋገጥ የመግቢያና መውጫ መልቀቂያ ፈቃድ መስጠት፣

#### 3.1.2 በኢንስፔክሽን ብቃታቸው የተረጋገጠ የምርምር፣ የኤክስቴሽንና የመካናይዘሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት

ለ 51 የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ብቃታቸውን የማረጋገጥና ስራ ይከናወናል።ከዚህ ጋር ተያይዞም ቀጣዮቹ ዝርዝር ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል።

- ✓ ለ18 ግብርና መሳሪያ አስመጪ፣ አምራች እና ላኪ ድርጅቶችን የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል።
- ✓ ለ 2 የግብርና ምርምር አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል።
- ✓ 4 የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል።
- ✓ ለ10 ግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል።
- ✓ ለ 8 ግብርና መሳሪያ አስመጪ፣ አምራች እና ላኪ ድርጅቶች ኢንስፔክሽን ይካሄዳል ።
- ✓ ለ 2ግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ኢንስፔክሽን ይካሄዳል ።
- ✓ 1 ግብርና ምርምር አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ኢንስፔክሽን ይካሄዳል ።
- ✓ 6 በግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ኢንስፔክሽን ይካሄዳል ።

### 3.2 የእጽዋት ግብዓቶች ምርቶች እና አገልግሎት ቁጥጥር ማጠናከር

#### 3.2.1 ፍቱንነቱ፣ደህንነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ የፀረ ተባይ እና የአፈር ማዳበሪያ

##### 3.2.1.1 ፍቱንነቱ፣ደህንነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ የፀረ ተባይ

- ✓ ለ121579 ሜትሪክ ቶን ፀረ ተባይ ፍቱንነትና ፣ደህንነትንና ጥራትን የማረጋገጥ ስራ ይከናወናል።

##### 3.2.1.2 ጥራቱ የተረጋገጠ የአፈር ማዳበሪያ

- ✓ ለ 2441854 ሜትረክ ቶን የአፈርማዳበረያ ጥራቱን የማረጋገጥ ስራ ይከናወናል።

**3.2.1.3 የብቅት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ድርጅቶች /195/**

- ✓ ለ 295 ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡

**3.2.1.4 በአካባቢ እና በጤና ላይ የሚደርሰውን ስጋቶች በጥናት መቀነስ**

- ✓ በአካባቢ እና በጤና ላይ የሚደርሰውን ስጋቶች በጥናት ስለመቀነስ የ2 ሰነድ ዝግጅት ይከናወናል፡፡

**3.2.1.5በመስክ ምርምር ፣ በዶዜር ግምገማ እና በቤተ-ሙከራ ፍቱንነቱ፣ ደህንነቱ ና ጥራቱ ተረጋግጦ የተመዘገበ ፀረ-ተባይ እና የአፈር ማዳበሪያ**

- ✓ ለ445 በመስክ ምርምር ፣ በዶዜር ግምገማ እና በቤተ-ሙከራ ፍቱንነቱ፣ ደህንነቱ ና ጥራቱ ተረጋግጦ የተመዘገበ ፀረ-ተባይ እና የአፈር ማዳበሪያ

3.2.2 ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ለውጭ እና ለሀገር ውስጥ ገበያ የቀረቡ የዕጽዋት ምርቶች

**3.2.2.1 ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ዕጽዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች**

ለ 960,000 ሜትሪክ ቶን የዕፅዋት ዉጤቶች ጤንነቱ፣ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ እንዲላክ ይረጋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ቀጣዮቹ ዝርዝር ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

- ✓ ለውጭ ገበያ በሚቀርቡ በተመረጡ 400,000 የግብርና ምርቶች ላይ የማፅጠንት/Fumigation/ክትትል ይደረጋል፡፡
- ✓ ወደ ውጪ ለሚወጣ 60,000የዕፅዋት ምርት የጤንነት ማረጋገጫ ሠርተፍኬት ይሰጣል፡፡
- ✓ ወደ ውጭ የሚላኩ ዕፅዋት እና የዕፅዋት ውጤቶች ተቀባይነታቸውን የማሳደግ እና የተቀባይ ሃገራትን ቅሬታ(Notification) የመቀነስ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡
- ✓ ለ60 የአበባ፣የአትክልትና ፍራፍሬ እርሻዎችን በየሩብ ዓመቱ የመስክ ቁጥጥርና ክትትል የማድረግና ሞያዊ ድጋፍ የመስጠት ስራ ይከናወናል፡፡
- ✓ ወደ አውሮፓ ህብረት በሚላኩ የሮዝ አበባ ምርቶችን 4 ጊዜ ውጫዊ ኦዲት የማድረግ ስራ ይከናወናል፡፡
- ✓ Xylella fastidiosa ጨምሮ ሌሎች የተቀባይ ሀገራትን መስፈርት ተደርጎ በተመረጡ የዕፅዋት ተባዮች ላይ በመስክ ዳሰሳ እና ቅኝት በማካሄድ እንዲሁም በላብራቶሪ እንዲመረመር በማድረግ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የመላክ ስራ ይከናወናል፡፡
- ✓ ከመስክ የተሰበሰቡ ናሙናዎች ከXylella fastidiosa በሽታ ነጻ መሆናቸውን በላብራቶሪ በPCR test ምርመራ በማድረግ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት መላክ ስራ ይከናወናል፡፡
- ✓ ለዕፅዋትና ዕፅዋት ዉጤቶች ተቀባይ ሀገር የተባይ ስጋት ትንተና ቴክኒካል መረጃ/ሰነድ የመላክ ስራ ይከናወናል፡፡

- ✓ ለጥራጥሬ እና ቅባት እህሎች አበጣሪ እና አቀነባባሪእና ለቡና አበጣሪ እና ላኪ ድርጅቶች የምርት ዝግጅት ጤንነት፣ጥራት አና የምግብ ደህንነት አስተዳደር ስርዓት ተከትለው መስራታቸውን በየሩብ ዓመቱ ክትትል ማድረግ፣
- ✓ በእፅዋት ምርት ጥራትና ደህንነት ከእርሻ እስከ ገበታ ለክልልና ከተማ አስተዳደር ተቆጣጣሪ ባለሙያዎች ስልጠና የመስጠትስራ ይከናወናል፡፡
- ✓ ለጥራጥሬ እና ቅባት እህሎች አበጣሪ, አቀነባባሪ እና ላኪ ድርጅቶች የምርት ዝግጅት ጤንነት፣ጥራት አና የምግብ ደህንነት አስተዳደር ስርዓት ተከትለው እንዲሰሩ ማድረግ፣
- ✓ ለቡና አበጣሪ እና ላኪ ድርጅቶች የምርት ዝግጅት ጤንነት፣ጥራት አና የምግብ ደህንነት አስተዳደር ስርዓት ተከትለው እንዲሰሩ ማድርግ ፣
- ✓ ወደ አውሮፓ የሚሄደውን የሰሊጥ ምርት የሳልሞኔላ የላብራቶሪ ምርመራ እንዲያካሂዱ ማድረግ፣
- ✓ ሀገራዊ የአመራረት ሰርተፍኬቶችን አሟልተው የሚገኙ ተቋማት (የመንግስትም ሆነ የግል ድርጅት) ሰርተፍኬት መስጠት፡፡

### 3.2.2.2 ጤንነቱ፣ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕፅዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች

ለ65,000 ሜትሪክ ቶን የዕጽዋት ውጤቶች የጤንነትና ጥራት ማረጋገጫ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም

- ✓ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡለ 2000 ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤቶችና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሳቁሶች የቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ ይሰጣል፡፡
- ✓ ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ1900 ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ዉጤቶች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሳቁሶች የሚገቡባቸውን መስፈርቶች ማሟላታቸው ከተረጋገጠ በኋላ የጉምሩክ ማስለቀቂያ ደብዳቤ ይሰጣል፡፡
- ✓ ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ አገር ውስጥ 10,000የገባ ዕፅዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶችየጥራት እና ደህንነት የደረጃዎች ዝግጅት ይካሄዳል፡፡
- ✓ የዕፅዋት ኳራንቲን ተባይ ወደ ሀገሪቱ ከመግባቱ በፊት መተንበይና ገብቶ ሲገኝ በአፋጣኝ የመቆጣጠሪያ ዘዴ በመጠቀም ተባዩ በአስቸኳይ እንዲጠፋ 2 ጊዜ ክትትል ይደረጋል፡፡
- ✓ በድህረ መግባት ኳራንቲን (Post Entry Quarantine) ማለፍ ያለባቸውን ዕፅዋት እና የዕፅዋት ውጤቶች 6 ጊዜ ክትትል ይደረጋል፡፡
- ✓ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ ዕፅዋትና የዕፅዋት ዉጤቶች የተባይ ስጋት ትንተና የመስክ የዳሰሳ 4 ጊዜ ጥናት ይካሄዳል፡፡
- ✓ ለዕፅዋት እና የዕፅዋት ውጤቶች የጥራት እና ደህንነት የደረጃዎች4 ጊዜ ዝግጅት ይካሄዳል፡፡

### 3.2.2.3 የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ድርጅቶች

ለ 680 ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም ቀጣዮቹ ዝርዝር ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

- ✓ የዕፅዋት እና የዕፅዋት ውጤት ወደ ውጪ ሀገር ለመላክና ለማስመጣት እንዲሁም በማጥንት ስራ ላይ ለተሰማሩ 200 አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች/ግለሰቦች አስፈላጊውን የቢሮና የመጋዘን ኢንስፔክሽን በማካሄድ የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡
- ✓ ከስራ ክፍሉ የብቃት ማረጋገጫ ስርተፊኬት ለተሰጣቸው 478 ተቋማት ተገቢውን የቢሮና የመጋዘን ኢንሰፔክሽን በማድረግ ሰርተፊኬታቸውን የማደስ ስራ ይከናወናል፡፡
- ✓ በዕፅዋትና የግብርና ምርቶችን ስራ ብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ 40 ለንግድ የሚሰሩ ድርጅቶች /ግለሰቦች በመስፈርቱ መሰረት እየሰሩ ስለመሆናቸዉ ክትትልና ግምገማ ይደረጋል፡፡

### 3.2.2.4 የእፀዋት ዝርያ ጥበቃና ዘር ጥራት ቁጥጥር

**በምርምር ቀርበው የተገመገሙ ዕጩ የዕፅዋት ዝርያዎች**

**ቁልፍ ተግባራት**

- ✓ ለ120 በምርምር የቀረቡ ዕጩ የዕፅዋት ዝርያዎችን ግምገማ ይካሄዳል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም ቀጣዮቹ ዝዝር ተግባራት ይከናወናሉ፡፤
- ✓ 78 የዕፅዋት ዝርያዎች ጥራትና ዉጤታማነታቸው ተረጋግጦ ይመዘገባሉ ይለቀቃሉ፡፡
- ✓ 1,662,303 ኩ/ል የአገር ውስጥ ዘር በቁጥጥር ሰንሰለት አልፎ ጥራቱን የማረጋገጥ ስራ ይከናወናል፡፡
- ✓ በቁጥር 300 ከውጪ የገባ ዘር ናሙና ጥራቱ በላብራቶሪ እንዲፈተሽ ይደረጋል፡፡
- ✓ 500,000 ኪሎግራም ከውጭ አገር ሚገባ ዘር በቁጥጥር ሰንሰለት አልፎ ጥራቱ ይረጋገጣል፡፡
- ✓ ለ30 ዘር ስራ የተሰማሩ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡

## 3.2.2.5 ደረጃውን የጠበቀ የእፀዋት ጥራት ምርመራ ላብራቶሪ አገልግሎት

**በላቦራቶሪ የጥራት ፍተሻ የተደረገላቸው የእጽዋት ዘር፣ እጽዋት ምርት እና የእጽዋት ውጤት ናሙናዎች**

ለ 340 ጥራቱ በላብራቶሪ እንዲፈተሽ ከውጪ የገባ ዘር ናሙና ብዛት ከዚህ ጋር ተያይዞ ቀጣዮቹ ዝርዝር ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

- ✓ 300 ጥራት በላቦራቶሪ ፍተሻ የተረጋገጠ ከውጭ ሀገር የገባ የእጽዋት ዘር ናሙና በላቦራቶሪ ፍተሻ ይደረጋል ፡፡
- ✓ 40 ከክልል በሚመጡ የተለያዩ የሰብል/የአትክልት ዱፕሊኬት (Duplicate) ናሙናዎች ላይ የተከናወኑ የንጽጽር የላብራቶሪ ፍተሻ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

ለ 40 ጤንነቱ፣ ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ለውጭ እና ለሀገር ውስጥ ገበያ የቀረቡ የዕጽዋት ምርቶችብዛት ከዚህ ጋር ተያይዞ ቀጣዮቹ ዝርዝር ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

- ✓ 20 ጥራትና ደህንነቱ በላቦራቶሪ ፍተሻ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ዕጽዋት እና የዕፅዋት ውጤቶች ማስገቢያ ፈቃድ ይሰጣል፡፡
- ✓ 20 ጥራትና ደህንነቱ በላቦራቶሪ ፍተሻ ተረጋግጦ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕፅዋት እና የዕፅዋት ውጤቶች ማስገቢያ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

### 3.2 የእንስሳት ግብዓቶች ምርቶች እና አገልግሎት ቁጥጥር ማጠናከር

#### 3.3.1 የእንስሳት ምርቶችን ጤንነት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ

##### 3.3.1.1 ጤንንነቱ ጥራቱና ደህንነቱ፣ ተረጋግጦ የተቀባይ ሀገራትን መስፈርት በማሟላት ለወጪ ገቢያ ብቁ ሆኖ የቀረበ ሥጋና ተረፈ ሥጋ፣

ወደ ውጭ ለሚላከ 25000ቶን ስጋና ተረፈ ሥጋ ደህንነት ጥራትና ጤንነቱን የማረገጋጥ ሰራ ይከናወናል፤

- ✓ በ ለ202500 የቁም እንስሳት የቅድመ ዕርድ ምርመራ ይከናወናል፤
- ✓ ለ147780 የድህረ ዕርድ ምርመራ ይከናወናል ፡፡
- ✓ ለ20000 ቶን ሥጋና ተረፈ ሥጋ፣ ጤንንነቱ ጥራቱና ደህንነቱ፣ ተረጋግጦ የተቀባይ ሀገራትን መስፈርት በሚሟላት ለወጪ ገቢያ ይቀርባል፡፡
- ✓ ለስጋና ተረፈ ስጋ 8000 ዓለም ዓቀፍ የጤና ማረጋገጫ ሰርፊኬት ይሰጣል፡፡
- ✓ 300 ጥራዝ ዓለም አቀፍ የጤና ሰርተፊኬት በማሳተም ይሠራጫል፡፡

##### 3.3.1.2 በእንሰሳት ሥጋ እና ተረፈ ሥጋ ማቀነባበሪያ ተቋማት ላይ ኦዲት ኢንስፔክሽን ማካሄድ

- ✓ 60 በእንስሳት ስጋ እና ተረፈ ስጋ ማቀነባበሪያ ተቋማት ላይ የኦዲት ኢንስፔክሽን ይካሄዳል፡፡

##### 3.3.1.3 የስጋና ተረፈ ስጋ አምራች ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት

- ✓ ለ16 የስጋና ተረፈ ስጋ አምራች ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

- ✓ አዲስ ለሚገቡ ኤክስፖርት ቄራወች /ተረፈ ምርት ማቀነባበሪያ ድርጅቶች ብቃት ከቦታ መጣ ጀምሮ ክትትልና ቅጥጥር በማድረግ ሲያልቁም መመዝገብና የብቃት ማረጋገጫ የመስጠት ሥራ ይከናወናል፡፡
- ✓ በየጊዜው በሚደረግ ኦዲት ኢንስፔክሽን ላይ ተመስርቶ ለ8000 ኤክስፖርት ቄራወችን ብቃት ይታደሳል፡፡

**3.3.1.4 ለኮሜርሽያል የእንሰሳት ምርት ማቀነባበሪያ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ መስጠት**

ለ91 የማዘጋጃ ቤትና የግል የአገር/ውስጥ ቄራዎችን ከክልሎች ጋር በመሆን መመዝገብና የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡

- ✓ ለ55 የእንሰሳት ምርቶችን (ወተት፣ ማር፣ እንቁላል፣ዓሣ) ለሚያቀናብሩና ለሚያደራጁ ድርጅቶች ከክልሎች ጋር በመሆን መመዝገብና የብቃት ማረጋገጫ መስጠት፣
- ✓ የእንሰሳት ምርቶች (ወተት፣ ማር፣ እንቁላል) ብቃት ማረጋገጫና ማደሻ መስፈርት ማውጣትና መተገበር፣

**3.3.1.5 በእንስሳት ምርት ናሙናዎች ላይ የተካሄደ የላቦራቶሪ ጥራትና ደህንነት ምርመራ አገልግሎት ለ730 ናሙናዎች ይሰራል፡፡**

- ✓ በእንስሳት ምርት ናሙናዎች ላይ የተካሄደ የላቦራቶሪ ጥራትና ደህንነት ምርመራ አገልግሎት ለ730 ናሙናዎች ይሰራል፡፡

**3.2.2 በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች**

- ✓ በቁጥር የ65000 ወደ ውጭ የሚላክ የቁም እንሰሳት ጥራቱና ጤንነት ይረጋገጣል፡፡
- ✓ በቁጥር የ573000 ወደ ውጭ የሚላክ የለማ እንቁላል ጤንነቱ እና ደህንነቱ ይረጋገጣል፥፡
- ✓ ለ200ቶን ማርና ሰም በኳራንቲን የቁጥጥር ስርአት ውስጥ አልፎ የቨተርነሪ ሳኒተሪ ሰተፍኬት ይሰጣል፡፡
- ✓ ለ 4500000 ያለቀለት ቆዳና ሌጦ የቨተርነሪ ሳኒተሪ ሰተፍኬት ይሰጣል፡፡
- ✓ ለ 738492 ወደ ሀገር የሚገባ የአንድ ቀን ጫጩትና የለማ እንቁላል ጤንነቱ እና ደህንነቱ ይረጋገጣል፡፡
- ✓ ለ350 ወደ ሃገር ውስጥ የሚገባ የተሸሸለ ዳልጋ ከብት ጤንነቱ እና ደህንነቱ ይረጋገጣል፡፡
- ✓ 160000 ወደ ዐገር ለሚገባ አባላዘር ጤንነቱ እና ደህንነቱ የማረጋገጥ ሥራ ይሰራል፡፡
- ✓ **ለቁም እንስሳት፣ የእንስሳት ምርቶች እና ለውጭ ንግድ የታቀዱ የእንስሳት ተረፈ ምርቶች ላይ 70 ኢንስፔክሽን ይደረጋል፡፡**

- ✓ ከውጭ በሚገቡ 4000 የእንስሳት ግብዓቶች (የአንድ ቀን ጫጩት፣የዘር ፈሳሽ ፣የለማ እንቁላል እና ጊደሮች) የእንስሳት ጤና እና የጥራት ደረጃዎችን የሚያሟሉ ስለመሆናቸው የላብራቶሪ ምርመራዎች ይደረጋሉ፡፡

**3.2.3** ወደ ውጭ የሚላኩ የቁም እንስሳትን ከዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና፣ ደህንነት እና የምግብ ደህንነት ደረጃዎች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ 160000 ናሙናዎች ላይ የላብራቶሪ ምርመራ ይደረጋል፡፡

**3.2.4 ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድኃኒት**

- ✓ ወደ ሀገር ውስጥ ለገባ ወይም ለተመረተ 3500 ቶን የእንሰሳት መድሃኒት ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ ይረጋግጣል፡፡
- ✓ 120 የእንስሳት መድሃኒት ተገምግሞ፣ በኢንስፔክሽን ስርዓትና በላቦራቶሪ ምርመራ ተረጋግጦ ይመዘገባል፡፡
- ✓ 380 የመድሃኒት ናሙዎችን ላይ የጥራት፣ ደህንነት እና ፈዋሽነት የላቦራቶሪ ምርመራ ይካሄዳል፡፡
- ✓ 410 የእንስሳት መድኃኒት አምራች፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡
- ✓ 580 የእንስሳት መድሃኒት እና ተቋማት ላይ ኢንስፔክሽን ይካሄዳል፡፡

**በመድኃኒት ምርት ናሙናዎች ላይ የተካሄደ የላቦራቶሪ ጥራትና ደህንነት ምርመራ አገልግሎት**

- ✓ 380 በመድኃኒት ምርት ናሙናዎች ላይ የተካሄደ የላቦራቶሪ ጥራትና ደህንነት ምርመራ መጠን የማረጋገጥ ሥራ ይከናወናል ፡፡

**3.2.5 ጥራትና ደህነቱ የተረጋገጠ የእንሰሳት መኖ**

3.3.4.1 **የመኖ ተቋማትና ባለሙያዎች የተሰጠ የብቃት ማረጋገጥ**

**ለ565 የመኖ ተቋማትና ባለሙያዎች** የብቃት ማረጋግጫ ይሰጣል፡፡

- ✓ ለ197የመኖ ንግድ ተቋም የብቃት ማረጋግጫ እድሳት ይደጋል፣፡
- ✓ ለ64 አዲስ እና ምትክ የመኖ ንግድ ተቋማት፣/መኖና የመኖ ጥሬ ዕቃ ማምረት፣ አስመጪነት፣ ጅምላ ንግድአና ላኪ/የብቃት ማረጋግጫ ይሰጣል፡፡
- ✓ ለ239 የእንሰሳስ መ"ና ባለሙያዎች የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት የማደስ ስራ ይሠራላል፡፡
- ✓ ለ65 በመኖ ንግድ ተቋማት ለሚሰሩ የመኖ ባለሙያዎች አዲስና ምትክ ምዝገባና የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፣

3.3.4.2 ጥራትና ደህንነቱ ተጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ መኖ እና የመኖ ግብዓት

- ✓ ለ7000 ቶን ወደ መኖ እና የመኖ ግብዓት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ በአንድ መስኮት አገልግሎት የማስገቢያ ፈቃድ ይሰጣል፡፡
- ✓ ለ6000 ቶን መኖና የመኖ ግብዓት ጥራቱና ደህንቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ በአንድ መስኮት አገልግሎት የመልቀቂያ ፈቃድ ይሰጣል፡፡
- ✓ ለ100 አዳዲስ የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር የሰነድ ፍተሻ በማካሄድ የመመዝገብ ስራ ይከናወናል፣
- ✓ ለ300 እንስሳት መኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ ለወጪ ንግድ በሲንግል ዊንዶው የቅድመ ማስወጫ ሰርተፊኬት ይሰጣል፣
- ✓ ለ15 የብቃት ማረጋገጫ ሳያስፈልጋቸው መኖና የመኖ ጥሬ ዕቃ ለማስገባትና ለማስወጣት ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ፈቃድ ይሰጣል፣

3.3.4.3 የእንሳሰት መኖ እና ተቋማት ላይ ኢንስፔክሽን ማካሄድ

313 የእንሳሰት መኖ እና ተቋማት ላይ ኢንስፔክሽን ይካሄዳል፤

- ✓ በ50 የእንስሳት መኖ አስመጪ ተቋማት ላይ በ 2ዙር ተቋማት ኢንስፔክሽን ይደረጋል፤
- ✓ በ 4 ተቋማት የእንስሳት የመኖ አከፋፋይ ተቋማት ላይ 2ዙር) ኢንስፔክሽን ላየ ይደረጋል፤
- ✓ በ20 የእንስሳት የመኖ ጥሬ ዕቃ አምራች ተቋማት ላይ 2 ዙር ኢንስፔክሽን ይከናወናል፥፡
- ✓ በ66 የእንስሳት የመኖ አምራች ተቋማት ላየ 2 ዙር ኢንስፔክሽን ይከናወናል፡፡
- ✓ የበ52 እንስሳት የመኖ ጥሬ ዕቃ ላኪ ተቋማት ላየ 2ዙር) ኢንስፔክሽን የደረጋል፡፡
- ✓ የእንስሳት መኖ ግብዓት አምራች ድርጅቶችን ወደ ሕጋዊ አሰራር ማስገባት
- ✓ ከመኖ ጥራትና ደህንነት አኳያ ከህዝብ ለሚቀርብ ጥቆማ ምላሽ ይስጣል፡፡
- ✓ 150 የመኖ ናሙና በመሰብሰብ ጥራትና ደህንነቱ የማረጋገጥ ሥራ ይከናወናል፡፡
- ✓ 300000 ቶን የተቀነባበረ የመኖ እና የመኖ ግብዓት ጥራቱና ደህንነቱ የማረጋገጥ ሥራ ይከናወናል፡፡
- ✓ 160 በመኖ ምርት ናሙናዎች ላይ የተካሄደ የላቦራቶሪ ጥራትና ደህንነት ምርመራ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

3.2.6 ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳት ጥራት ምርመራ ላብራቶሪ አገልግሎት

የእንስሳት ውጤቶች ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ

- ✓ የጥራት ማኔጅመንት ስርዓት ትግበራ ሥራዎችን በማጠናከር እውቅና የተገኘባቸውን 13 የላቦራቶሪ ምርመራ ሥራዎችን የማስቀጠል ስራ ይከናወናል፡፡

## 4. ተቋማዊ የመፈፀም አቅም፣ ውጤታማ የሀብት አጠቃቀምና አገልግሎት አሰጣጥ እና የህግ ማዕቀፎች

### 4.1 የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማጠናከር

- ✓ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ሬጉላቶሪ ስርዓትን ለማጠናከር እና ተግባራዊ ለማድረግ ለክፍሉ ለ16 ባለሙያዎች የተለያዩ ስልጠናዎችን መስጠት፡፡
- ✓ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ሬጉላቶሪ ስራዎችን በማዕከላትና ጣቢያ 2 ዙር ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፡፡
- ✓ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ተቋማትን3 መረጃ ሰነድ ማሰባሰብንና ማደራጀት፡፡
- ✓ ወደ ሀገር የሚገቡ የግብርና መሳሪያዎች1 መረጃ ማደራጀት፡፡
- ✓ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ሬጉላቶሪ ስራዎችን ለማሳለጥ 3የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፡፡
- ✓ ኳራንታይንና ሬጉላቶሪ እና ለክልል ሬጉላቶሪ ለ 60 ባለሙያዎች በሚጸድቀው የዕፅዋት ጥበቃና ራንቲን አዋጅ እና በሌሎች የህግ ማዕቀፎች ላይ ስልጠና መስጠት፡፡
- ✓ ኳራንታይንና ሬጉላቶሪ ለ 40 ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፡፡
- ✓ በእፅዋት ምርት ጥራትና ደህንነት ከእርሻ እስከ ገበታ ለክልልና ከተማ አስተዳደር ተቆጣጣሪ ለ 70 ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት፡፡
- ✓ ለጥራጥሬ እና ቅባት እህሎች አበጣሪ እና አቀነባባሪእና ለቡና አበጣሪ እና ላኪ ድርጅቶች በምግብ ደህንነት አስተዳደር ስርዓት ላይ ፡ ብሄራዊ እና አለምአቀፍ ደረጃዎች ላይ 2 መድረክ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና ስልጠና መስጠት
- ✓ ለእንስሳት ምርት ጥራትና ጤንነት ደህንነት ላይ ለሚሰሩ የኢንስፔክሺንና ሰርተፊኬሺን ባለሙያዎች እያደገ የሚሄድ የአቅም ግንባታ ለ250 ባለሙያ ሥልጠና መስጠት፡፡
- ✓ የ6 ወይም የ3 ወራት የስጋ ምርመራ ስልጠና ከፕሮጀክቶች ጋር በመተባበር ለ30 ባለሙያዎች አሰልጥኖ የተመሰከረላቸው ስጋ መርማሪ ማድረግ፡፡
- ✓ ስለ እንስሳት ምርት ጥራትና ደህንነት ላይ የተሻለ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስላጠና ለ40 ባለድርሻ አካላት መስጠት፡፡
- ✓ ለ12 ላቦራቶሪ ቴክኒሻኖች ስለ ላቦራቶሪ ምርመራ ዘዴዎች ከሰበታ ላቦራቶሪ ጋር በመተባበር የተሀድሶ ሥልጠናው እንዲሰጣቸው ማድረግ፣
- ✓ ለእንስሳት ውጤቶች ጤንነትና ደህንነት ቁጥጥር እና የስጋ ምርመራና ሃይጂን የፀደቀ ደንብን ለባለድርሻ አካላት ግንዛቤ ማስጨበጥና ተግባራዊ ማድረግ ፡፡ እንዲሁም የስጋና

የሌሎች የእንስሳት ውጤቶች ምርመራ ረቂቅ መመሪያ አንድ (1) ማዘጋጀትና ለማጸደቅ ማቅረብ፡፡

- ✓ በበጀት ዓመቱ (2018 ዓ/ም) ዓለም ዓቀፍ የጤና ማረጋገጫ ሰርተፊኬት 300 ጥራዝ ማሳተምና የማሰራጨት፡፡

## 4.2 የክትትልና ግምገማ ስርዓት

- ✓ የሥጋ ቅዝቃዜና ጥራትን በተመለከተ ከቄራዎች ጀምሮ እስከ ቦሌ ፍረሽ ፖርት ድረስ የሚገኘውን የጥራት ሁኔታ ለማሻሻል የተዘረጋውን የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት ላይ 3 ጊዜ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ፣መረጃውን በመተንተን ለሚመለከታቸው አካላት ማሰራጨት፣
- ✓ በየሩብ ዓመቱ በኤክስፖርት ቄራዎች ግምገማ ፣ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ እንዲሁም ግብረ መልስ በመስጠት እያደገ የሚሄድ የኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን አገልግሎት መገንባት፡፡
- ✓ የማዘጋጃ ቤትና የግል የአገር ውስጥ ቄራዎች የሚቀርበውን ሥጋና ተረፈ ስጋ ምርት እና ሌሎች የእንስሳት ምርቶችን (ወተት፣ ማር፣ እንቁላል) ጤንነት፣ ጥራት እና ደህንነትን የክትትልና የቁጥጥር ስራ በዓመቱ  ውስጥ ሁለት ጊዜ በማድረግ ለሚመለከታቸው አካላት ግብረ መልስ በመስጠት እያደገ የሚሄድ የምግብ ጤንነት፣ ጥራትና ደህንነት ስርዓትን መዘርጋት፡፡

### 4.3 ተግባራዊ የተደረገ የህግ ማዕቀፍ

- ✓ 2 የተዘጋጁ የግብርና ሜካናይዜሽን መመሪያዎችን የማጸደቅ
- ✓ 2 ተጨማሪ የግብርና ሜካናይዜሽን መመሪያዎችን ማዘጋጀት
- ✓ የተዘጋጀውን ረቂቅ የዕፅዋት ጥበቃና ▯ራንቲን አዋጅ እንዲፀድቅ ክትትል ማድረግ፣
- ✓ የምግብ ደህንነት አዋጅና ደንብ ማዘጋጀት፡፡
- ✓ ረቂቅ የዕፅዋት ▯▯ራንቲን ደንብ  የሕግ ማዘጋጀት፡፡
- ✓ የዕፅዋትና  የግብርና  ምርቶችን የማዘጋጀት፣ ማከማቸትና የማከም የብቃት ማረጋገጫ መመሪያ አጠናቆ ለባሊዴሽን ማቅረብ፡፡
- ✓ ሀገራዊ የአመራረት፣ የአሰባሰብ ፣የማጓጓዝ፡ የአያያዝ ሰርተፍኬቶችን ከአለም አቀፍ ጋር በማገናኘት ማዘጋጀት አሟልተው የሚገኙ ተቋማት (የመንግስትም ሆነ የግል ድርጅት) ሰርተፍኬት መስጠት መሰፈርት ማዘጋጀት፡፡
- ✓ የዕፅዋት  ካ▯▯ራንቲን  ተባይ ዝርዝር ማሻሻል/ Updating Quarantine pest list/
- ✓ የተዘጋጀውን  PRA document ማሳተም፡፡
- ✓ PRA operational procedure ማዘጋጀት፡፡

- ✓ የSystem approach Implementation and audit Procedure ማዘጋጀት
- ✓ የPhytosanitary Export Inspection and Certification Standard Operation Procedure (SOP) ማሻሻል፡፡
- ✓ ጣቢያዎች ያሉበትን ደረጃ በመገምገም ሊያሰራ የሚችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት
- ✓ አንድ የዕፅዋት ▯▯▯ራንቲን የስልጠና ማኑዋል ማዘጋጀት፡፡
- ✓ የ እጽዋት ምርት ሳኒተሪ እና ፋይቶ ሳኒተሪ ስራን የሚያጠናክሩ ፕሮጀክቶችን ማዘጋጀት

## 4.4 በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (Digitalization) የታገዘ አገልግሎት

- ✓ የፋይቶ ሳኒታሪ ሰርተፊኬሽን (ePhyto) ስራ ዲጅታላይዝ የማድረግ ስራ ይከናወናል ፡፡
- ✓ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬትን ሙሉ በሙሉ ዲጂታላይዝ የማድረግ ስራ ይከናወናል ፡፡
- ✓ በሰራ ክፍሉ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለመረጃነት እንዲያገለግሉ ወደ መረጃ ቋት በማስገባት ማረጋገጥ እንዲሁም ብሔራዊ የመረጃ ቋት ስርዓት የመዘርጋት ስራ ይከናወናል ፡፡

1. **የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት ማሻሻል**
   - ✓ የሰው ሀብት አስተዳደር ማጉልበት ሥራ ይከናወናል፡፡
   - ✓ የሰው ሀይል አቅም የመገንባት ሥራ ይከናወናል፡፡
   - ✓ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት የማሣደግ ሥራ ይከናወናል፡፡
   - ✓ የሪከርድና ማህደር በዘመናዊ መልኩ ማደራጀትና የማዘመን ሥራ ይከናወናል፡፡
2. **የስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ሪፖርት ዝግጅት፣ ክትትል፣ ግምገማ እና ግብረ-መልስን ማሻሻል**
   - ✓ የስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ሪፖርት ዝግጅት፣ ክትትል፣ ግምገማ እና ግብረ-መልስን የማሻሻል ሥራ ይከናወናል፡፡
   - ✓ ክትትል ግምገማ ስርዓት መዘርጋ እናተግባራዊ የማድረግ ሥራ ይከናወናል፡፡
   - ✓ አጋትነት እና ሃብት የማሰባብ ሥራ ይከናወናል፡፡
   - ✓ ዶክመንት ዝግጅት እና መረጃ አያያዝን የማሻሻል ሥራይከናወናል፡፡
3. **ተግባራዊ የተደረገ የህግ ማዕቀፍ**
   - ✓ የባለስልጣኑ ሥራዎች በሕግ አግባብ እንዲሰሩ የማድረግ ሥራ ይከናወናል፡፡
   - ✓ ባለስልጣን መ/ቤቱን ወክሎ ክርክር የማድረግ ሥራ ይከናወናል፡፡
   - ✓ ለግብርና ቁጥጥር የህግ ግንዛቤን የተሳለጠ የማድረግ ሥራ ይከናወናል፡፡
   - ✓ በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚካሄዱ ከህግ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥናቶችና ውይይቶች ላይ በመሳተፍ ለቁጥጥር ተግባሩ የሚውል የህግ ነክ የግብዓት ሥራ ይከናወናል፡፡
   - ✓ የሕግ አገልግሎትን አጠቃቀም የማጎልበት ሥራ ይከናወናል፡፡
   - ✓ የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓትን የማሻሻል ሥራ ይከናወናል፡፡
   - ✓ የሥራ አመራር ስርዓት የማጎልበትሥራ ይከናወናል፡፡

4. **የፋይናንስና ግዥና  አስተዳደር**
   - ✓ የዘመነ የገቢና ክፍያ ስርዓት ማሳደግ
   - ✓ የዘመነ የግዢ አገልግሎት ማሰደግ
   - ✓ ከግኝትነና ከቅሬታ የጸዳ የአሠራር ሥርዓትን መዘርጋት
5. **መሰረታዊ አገልግሎትን በቅልጥፍና በመስጠት የደንበኞችን እርካታ ማሻሻል**
   - ✓ ለ 200,432 የኤሌክትሮኒክስ የንብረት ቁጥጥር አሰራር ይተገበራል፡፡
   - ✓ ለ 4320 የተሽከርካሪ ስምሪት ስራን የማጎልበት ሥራ ይከናወናል፡፡
   - ✓ የንብረት አያያዝ እና የጥገና ወጪዎችን መቀነስ
6. **የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ለውጤታማነትን ማሻሻል**
   - ✓ የተመሰረተ የመረጃ ስርዓት ሲስተም የመዘርጋት ሥራ ይከናወናል፡፡
   - ✓ የተመሠረተ ወረቀት አልባ ስርዓት የመዘርጋት ሥራ ይከናወናል፡፡
   - ✓ ያደገ አውቶሜትድ ያሠራር ስርዓት የማሳደግ ሥራ ይከናወናል ፡፡
   - ✓ የሲስተም አስተዳደርና ድጋፍ ስራ የማከናወን ሥራ ይከናወናል ፡፡
7. **ተቋማዊ የሪፊርም ሥርዓት በመጠቀም የተገልጋዮችን እርካታ ደረጃ ማሳደግ**
   - ✓ አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃና የተገልጋይ እርካታን ማሳደግ
   - ✓ 8 ከተገልጋዮች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የቅሬታ አፈታት አሰራር ሥርዓት መሰረት ማጣራት እና ተገቢውን ምላሽ መሥጠት፤
   - ✓ መጠይቆችን በማዘጋጀት የተገልጋዮች እርካታ ደሰሳ ጥናት ማካሄድ፣መረጃውን መተንተንና ከተገልጋዮች በሚሰጥ ግብረ መልስ መሰረት የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ እንዲሻሻል ማድረግ፤
   - ✓ ተቋማዊ ካይዘን ሥርዓት የመተግበር ሥራ ይከናወናል፡፡
   - ✓ የለውጥ ሥራ አመራርና የአሠራር ማሻሻያ ስልቶችን ተግባራዊ የማድረግ ሥራ ይከናወናል፡፡
   - ✓ ለ 7 ተቋማዊ ለውጥ በቀጣይነት ለመተግበር እንዲችል የክህሎት፣ የአቅርቦት እና የአመለካከት ክፍተቶችን የመለየትና የመፍታት ሥራ ይከናወናል፡፡
8. **አጋርነትና ህዝብ ግንኙነት**
   - ✓ የገፅ ለገፅ፤ የህትመትና የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎችን በመጠቀም መረጃዎችን ለህብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ
   - ✓ ሶሻል ሚዲያውን አይቶ ወደ ተግባር እንዲገባ የሚያስችል መልእክት መተላለፉ፣
   - ✓ ሁነቶችን በማደራጀት ስኬቶችን ማስታዋወቅና መግባባትን መፍጠር

9. ስነ ምግባርና የፀረ ሙስና
   - ✓ የሥነ-ምግባር ግንባታ ውጤታማነት የማሳደግ ሥራ ይከናወል፡፡
   - ✓ የሙስና ተጋላጭነት እና ስጋትን የመቀነስ ሥራ ይከናወል፡፡
   - ✓ የሙስና መረጃ አስተረዳደር ውጤታማነትን ማረጋገጥ

10. ማህበራዊ አካታችነትና የሴቶች ተጠቃሚነት
   - ✓ የሴቶች እና ወጣቶች አቅም በመገንባትና እኩል ተጠቃሚነታቸውን በማሳድግ ለቁጥጥር ተግባሩ ያላቸውን ሚና ማጐለበት፡፡
   - ✓ የሴቶች፣ የህጻናት፣ የወጣቶች እና ተጋላጭ የሆኑ ቡድኖች ተሳትፎን ማስፋፋት፡፡
   - ✓ የአካባቢ እና ማህበራዊ  ተፅዕኖ  መቀነሻ ስርዓቶችን አተገባበር የመከታተል ሥራ ይከናወል፡፡

| የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የ2017 ዕቅድ በቁልፍ አመልካቾች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቁልፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ የ2017 አፈጻጸም | የ2018 ዕቅድ | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛሩብ ዓመት |
| ንዑስ ፕሮግራም :-በዕጽዋትና ከዕጸጽዋት ጋር በተገናኙ ግብዓቶች፣ ምርቶች፣ ቴክኖሎጂ እና አገልግሎቶች ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር ማጠናከር | | | | | | | |
| ፍቱንነቱ፣ደህንነቱ እና ጥራቱ የተረጋገጠ ፀረ-ተባይ እና ማዳበሪያ | | | | | | | |
| ፍቱንነቱ፣ደህንነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ የፀረ ተባይ | ቶን | 111237 | 121579 | 38905 | 30394 | 19452 | 32828 |
| ጥራቱ የተረጋገጠ የአፈር ማዳበሪያ | ቶን | 2035774 | 2441854 | 366279 | 488370 | 732557 | 854648 |
| የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ድርጅቶች | ቁጥር | 231 | 295 | 95 | 85 | 65 | 50 |
| በአከባቢ እና በጤና ላይ የሚደርሰውን ስጋቶችን በጥናት መቀነስ | በሰነድ | 2 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| በመስክ ምርምር ፣ በዶዜር ግምገማ እና በቤተ-ሙከራ ፍቱንነቱ፣ ደህንነቱ ና ጥራቱ ተረጋግጦ የተመዘገበ ፀረ-ተባይ እና የአፈር ማዳበሪያ | በቁጥር | 411 | 445 | 105 | 130 | 105 | 105 |
| ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ለውጭ እና ለሀገር ውስጥ ገበያ የቀረቡ የዕጽዋት ምርቶች | | | | | | | |
| ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ዕጽዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች | ሜ/ቶን | 872750 | 960000 | 240000 | 240000 | 240000 | 240000 |
| ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕፅዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች | ሜ/ቶን | 87020 | 65000 | 16250 | 16250 | 16250 | 16250 |
| የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ድርጅቶች | ቁጥር | | 680 | 171 | 169 | 171 | 169 |

| የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የ2017 ዕቅድ በቁልፍ አመልካች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ቁልፍ አመልካቾች** | መለኪያ | መነሻ የ2017 አፈጻጸም | የ2018 ዕቅድ | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛሩብ ዓመት |
| **የዕጽዋት ዝርያ ጥበቃ እና ዘር ጥራት ቁጥጥር** | | | | | | | |
| በምርምር ቀርበው የተገመገሙ ዕጩ የዕፅዋት ዝርያዎች | ቁጥር | 153 | 120 | 10 | 60 | 40 | 10 |
| ጥራትና ዉጤታማነታቸው ተረጋግጦ የተመዘገቡና የተለቀቁ የዕፅዋት ዝርያዎች | ቁጥር | 97 | 78 | | | 60 | 18 |
| በቁጥጥር ሰንሰለት አልፎ ጥራቱ የተረጋገጠ የአገር ውስጥ ዘር | ኩንታል | 816891 | 1,662,303 | | | 1,163,612 | 498691 |
| በቁጥጥር ሰንሰለት አልፎ ጥራቱ የተረጋገጠ ከውጭ አገር የገባ ዘር መጠን ውስጥ ለላብራቶሪ የቀረበ የናሙና ብዛት | ቁጥር | 420 | 300 | 60 | 80 | 80 | 80 |
| በቁጥጥር ሰንሰለት አልፎ ጥራቱ የተረጋገጠ ከውጭ አገር የገባ ዘር | ኩንታል | 439003 | 500,000 | 100000 | 150000 | 150000 | 100000 |
| የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ድርጅቶች | ቁጥር | 31 | 30 | 5 | 10 | 10 | 5 |
| **በላቦራቶሪ የጥራት ፍተሻ የተደረገላቸው የእጽዋት ዘር፣ እጽዋት ምርት እና የእጽዋት ውጤት ናሙናዎች** | | | | | | | |
| ጥራቱ በላብራቶሪ እንዲፈተሽ ከውጪ የገባ ዘር ናሙና ብዛት | | | 340 | 70 | 90 | 90 | 90 |
| ጥራት በላቦራቶሪ ፍተሻ የተረጋገጠ ከውጭ ሀገር የገባ የእጽዋት ዘር ናሙና | ቁጥር | 396 | 300 | 60 | 80 | 80 | 80 |
| ከክልል በሚመጡ የተለያዩ የሰብል/የአትክልት ዱፕሊኬት (Duplicate) ናሙናዎች ላይ የተከናወኑ | ቁጥር | 28 | 40 | 10 | 10 | 10 | 10 |

| የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የ2017 ዕቅድ በቁልፍ አመልካች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ቁልፍ አመልካቾች** | መለኪያ | መነሻ የ2017 አፈጻጸም | የ2018 ዕቅድ | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛሩብ ዓመት |
| የንጽጽር የላብራቶሪ ፍተሻ ስራዎች | | | | | | | |
| ጤንነቱ፣ ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ለውጭ እና ለሀገር ውስጥ ገበያ የቀረቡ የዕጽዋት ምርቶች | | | 40 | | | 20 | 20 |
| ጥራትና ደህንነቱ በላቦራቶሪ ፍተሻ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ዕጽዋት እና የዕፅዋት ውጤቶች | ቁጥር | – | 20 | | | 10 | 10 |
| ጥራትና ደህንነቱ በላቦራቶሪ ፍተሻ ተረጋግጦ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕፅዋት እና የዕፅዋት ውጤቶች | ቁጥር | – | 20 | | | 10 | 10 |
| **ውጤታማነቱ፣ ጥራቱና ተስማሚነቱ የተረጋገጠ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ** | | | | | | | |
| ውጤታማነቱ ተረጋግጦ የብቃት ማረጋገጫ ያገኙ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ | በቁጥር | | 10 | | 1 | 3 | 6 |
| በኢንስፔክሽን ብቃታቸው የተረጋገጠ የምርምር፣ የኤክስቴሽንና የመካናይዘሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት | በቁጥር | | 34 | | 4 | 13 | 17 |
| **ንዑስ ፕሮግራም፡- የእንስሳትና ከእንስሳት ጋር የተገናኙ የግብዓቶች፣ ምርቶች፣ ቴክኖሎጂ እና አገልግሎቶች ቁጥጥር ማጠናከር** | | | | | | | |
| **የእንስሳት ምርቶችን ጤንነት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ** | | | | | | | |
| ደህንነቱ ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ስጋና ተረፈ ሥጋ | በቶን | 21,200.30 | 25,000 | 6,000 | 6,500 | 6,500 | 6,000 |

| የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የ2017 ዕቅድ በቁልፍ አመልካቾች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ቁልፍ አመልካቾች** | መለኪያ | መነሻ የ2017 አፈጻጸም | የ2018 ዕቅድ | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛሩብ ዓመት |
| የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኙ የስጋና ተረፈ ስጋ አምራች ተቋማት | በቁጥር | 15 | 16 | | 16 | | |
| ጥራቱና ደህንነቱ በላቦራቶሪ ፍተሻ የተረጋገጠ የእንስሳት ምርት ናሙናዎች | በቁጥር | 670 | 730 | 180 | 183 | 183 | 182 |
| ለኮመርሻል የእንስሳት ምርት ማቀነባበሪያ ድርጅቶች የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ | በቁጥር | 72 | 91 | | 45 | | 46 |
| በእንስሳት ሥጋ እና ተረፈ ሥጋ ማቀነባበሪያ ተቋማት ላይ የተካሄደ ኢንስፔክሽን | በቁጥር | 60 | 60 | 15 | 15 | 15 | 15 |
| **በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች** | | | | | | | |
| ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ የቁም እንስሳት | ቁጥር | 621,000 | 650,000 | 157,000 | 159,000 | 164,000 | 170,000 |
| ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ የለማ እንቁላል | በቁጥር | 4,764,449 | 573,000 | 142,000 | 140,000 | 145,0,00 | 146,000 |
| ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ሰምና ማር | በቶን | 270 | 200 | 45 | 58 | 50 | 47 |
| ጥራቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ቆዳና ሌጦ | በቁጥር | 4,694,016 | 4,500,000 | 1,100,000 | 1,100,000 | 1,200,000 | 1,100,000 |
| ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር የገባ የአንድ ቀን ጫጩትና የለማ እንቁላል | በቁጥር | 733,662 | 738,492 | 184,000 | 185,246 | 184,000 | 185,246 |

| የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የ2017 ዕቅድ በቁልፍ አመልካቾ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ቁልፍ አመልካቾች** | መለኪያ | መነሻ የ2017 አፈጻጸም | የ2018 ዕቅድ | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛሩብ ዓመት |
| ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር የገባ የተሻሻለ ዳልጋ ከብት | ቁጥር | 793 | 350 | 80 | 85 | 90 | 95 |
| ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር የገባ አባላዘር | ዶዝ | 152,146 | 160,000 | 40,000 | 40,000 | 40,000 | 40,000 |
| ለቁም እንስሳት፣ የእንስሳት ምርቶች እና ለውጭ ንግድ የታቀዱ የእንስሳት ተረፈ ምርቶች ላይ ለመከናወን የተቀዱ ኢንስፔክሽን | ቁጥር | 50 | 70 | 16 | 17 | 18 | 19 |
| የእንስሳት ጤና እና የጥራት ደረጃዎችን የሚያሟሉ የላብራቶሪ ምርመራዎች ብዛት ከውጭ ለሚገቡ የእንስሳት ግብዓቶች (የአንድ ቀን ጫጩት፣የዘር ፈሳሽ ፣የለማ እንቁላል እና ጊደሮች) ብዛት | ቁጥር | - | 4000 | 500 | 1200 | 1100 | 1200 |
| ከዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና፣ ደህንነት እና የምግብ ደህንነት ደረጃዎች ጋር የተጣጣሙ የቁም እንስሳትን ወደ ውጭ ለመላክ የሚደረጉ የላብራቶሪ ምርመራዎች | በናሙና ቁጥር | - | 160000 | 40000 | 40000 | 40000 | 40000 |
| **ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድኃኒት** | | | | | | | |
| ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ወይም የተመረተ የእንስሳት መድሃኒት | በቶን | 2850 | 3500 | 850 | 850 | 850 | 850 |

| የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የ2017 ዕቅድ በቁልፍ አመልካቾች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ቁልፍ አመልካቾች** | መለኪያ | መነሻ የ2017 አፈጻጸም | የ2018 ዕቅድ | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛሩብ ዓመት |
| ተገምግሞ፣ በኢንስፔክሽን ስርዓትና በላቦራቶሪ ምርመራ ተረጋግጦ የተመዘገበ የእንስሳት መድሃኒት | በቁጥር | 75 | 120 | 30 | 30 | 30 | 30 |
| የመድሃኒት ናሙዎችን ላይ የተካሄደ የጥራት፣ ደህንነት እና ፈዋሽነት የላቦራቶሪ ምርመራ | በቁጥር | 315 | 380 | 95 | 95 | 95 | 95 |
| የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኙ የእንስሳት መድኃኒት አምራች፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት | በቁጥር | 375 | 410 | 71 | 268 | 35 | 36 |
| የእንስሳት መድሃኒት እና ተቋማት ላይ የተካሄደ ኢንስፔክሽን | በቁጥር | 629 | 580 | 144 | 147 | 145 | 144 |
| **ጥራቱና ደህንነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መኖ** | | | | | | | |
| የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኙ መኖ አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት | በቁጥር | 454 | 565 | 228 | 170 | 119 | 48 |
| ጥራቱና ደህንቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ወይም የተመረተ መኖ እና የመኖ ግብዓት | በቶን | 7320 | 7000 | 1500 | 2000 | 2000 | 1500 |
| በእንስሳት መኖ እና ተቋማት ላይ የተካሄደ ኢንስፔክሽን | በቁጥር | 244 | 384 | 65 | 119 | 112 | 88 |

| የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የ2017 ዕቅድ በቁልፍ አመልካች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ቁልፍ አመልካቾች** | መለኪያ | መነሻ የ2017 አፈጻጸም | የ2018 ዕቅድ | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛሩብ ዓመት |
| ለጥራትና ደህንነት ፍተሻ የተሰበሰበ የመኖ ናሙና | ናሙና ብዘት | | 150 | 30 | 40 | 40 | 40 |
| ጥራቱና ደህንቱ ተረጋግጦ  የተመረተ የተቀነባበረ መኖ | በቶን | 205370 | 300000 | 75000 | 75000 | 75000 | 75000 |
| የመኖ እና የመኖ ጥሬ ግብዓት ናሙናዎች ላይ የተካሄደ የጥራት እና ደህንነት የላቦራቶሪ ምርመራ | በቁጥር | 93 | 160 | 40 | 40 | 40 | 40 |
| **ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳትና የዕጽዋት ጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ አገልግሎት** | | | | | | | |
| የጥራት ማኔጅመንት ስርዓት ትግበራ ሥራዎችን በማጠናከር እውቅና የተገኘባቸውን 13 የላቦራቶሪ ምርመራ ሥራዎችን ማስቀጠል | በመቶኛ | 100% | 100% | 25% | 25% | 25% | 25% |
| **የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት ማሻሻል** | | | | | | | |
| የሰው ሀብት አስተዳደር ማጉልበት | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| የሰው ሀይል አቅም መገንባት | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት ማሣደግ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

| የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የ2017 ዕቅድ በቁልፍ አመልካቾ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ቁልፍ አመልካቾች** | መለኪያ | መነሻ የ2017 አፈጻጸም | የ2018 ዕቅድ | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛሩብ ዓመት |
| የሪከርድና ማህደር በዘመናዊ መልኩ ማደራጀትና ማዘመን | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| **የስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ሪፖርት ዝግጅት፣ ክትትል፣ ግምገማ እና ግብረ-መልስን ማሻሻል** | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| የስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ሪፖርት ዝግጅት፣ ክትትል፣ ግምገማ እና ግብረ-መልስን ማሻሻል | በሰነድ | | 12 | 4 | 4 | 2 | 2 |
| ክትትል ግምገማ ስርዓት መዘርጋ እናተግባራዊ ማድረግ | በጊዜ | | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| አጋትነት እና ሃብት ማሰባብ | ሰነድ | | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| ዶክመንት ዝግጅት እና መረጃ አያያዝን ማሻሻል | በሰነድ | | 6 | 1 | 2 | 1 | 2 |
| **ተግባራዊ የተደረገ የህግ ማዕቀፍ** | | | | | | | |
| | | | | | | | |

| የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የ2017 ዕቅድ በቁልፍ አመልካቾ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ቁልፍ አመልካቾች** | መለኪያ | መነሻ የ2017 አፈጻጸም | የ2018 ዕቅድ | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛሩብ ዓመት |
| የባለስልጣኑ ሥራዎች በሕግ አግባብ እንዲሰሩ ማድረግ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| ባለስልጣን መ/ቤቱን ወክሎ ክርክር ማድረግ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| ለግብርና ቁጥጥር የህግ ግንዛቤን የተሳለጠ ማድረግ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚካሄዱ ከህግ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥናቶችና ውይይቶች ላይ በመሳተፍ ለቁጥጥር ተግባሩ የሚውል የህግ ነክ ግብዓት | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| የሕግ አገልግሎትን አጠቃቀም ማጎልበት | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓትን ማሻሻል ፡ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| የሥራ አመራር ስርዓት ማጎልበት | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| **የፋይናንስና ግዥ አስተዳደር ማሻሻል** | | | | | | | |
| የዘመነ የገቢና ክፍያ ስርዓት | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

| የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የ2017 ዕቅድ በቁልፍ አመልካቸ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ቁልፍ አመልካቾች** | መለኪያ | መነሻ የ2017 አፈጻጸም | የ2018 ዕቅድ | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛሩብ ዓመት |
| የዘመነ የግዢ አገልግሎት | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| ከግኝትነና ከቅሬታ የጸዳ አሠራር | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| መሰረታዊ አገልግሎትን በቅልጥፍና በመስጠት የደንበኞችን እርካታ ማሻሻል | | | | | | | |
| የኤሌክትሮኒክስ የንብረት ቁጥጥር አሰራር መተግበር | በቁጥር | 190432 | 200,432 | 50,083 | 50,113 | 50,268 | 50,078 |
| የተሽከርካሪ ስምሪት ስራን ማጎልበት | በቁጥር | 4159 | 4320 | 1058 | 1068 | 1072 | 1122 |
| የንብረት አያያዝ እና የጥገና ወጪዎችን መቀነስ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| **የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ለውጤታማነትን ማሻሻል** | | | | | | | |
| የተመሰረተ የመረጃ ስርዓት | **በቁጥር** | | **3** | | | **1** | **2** |
| የተመሠረተ ወረቀት አልባ ስርዓት | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

| የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የ2017 ዕቅድ በቁልፍ አመልካቾ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቁልፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ የ2017 አፈጻጸም | የ2018 ዕቅድ | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛሩብ ዓመት |
| ያደገ አውቶሜትድ ያሠራር ስርዓት | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| የሲስተም አስተዳደርና ድጋፍ ስራ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| **ተቋማዊ የሪፎም ሥርዓት በመጠቀም የተገልጋዮችን እርካታ ደረጃ ማሳደግ** | | | | | | | |
| የተገልጋይን እርካታ ማሳደግ | በመቶኛ | 85 | 87 | | 85 | 86 | 87 |
| በተቋሙ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መፍታት | በቁጥር | 8 | 8 | 2 | 2 | 2 | 2 |
| ግልፅነት የሰፈነበት የአገልግሎት አሰጣጥ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| ተቋማዊ ካይዘን ሥርዓት መተግበር | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| ቀጣይነትና ተከታታይነት ያለውየለውጥ ስርዓት | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| የቀጠለ የተቋማዊ ለውጥ ግንዛቤ | በቁጥር | 3 | 7 | 1 | 3 | 3 | |

| የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የ2017 ዕቅድ በቁልፍ አመልካቾች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቁልፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ የ2017 አፈጻጸም | የ2018 ዕቅድ | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛሩብ ዓመት |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |